# ሐዋርያዊ መልሶች - Apostolic Answers

## ተከታታይ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት መስጫ አጭር አጋዥ ጽሑፍ - 2

## ፈጣሪን እንዴት ማወቅ እንችላለን..?? | የእግዚአብሔር መገለጥ

እንደ ክርስትና ፈጣሪን በባህሪው(οὐσία – essence) የሚያውቀው ማንም የለም። በመጽሐፈ ኢዮብ 11:7 ላይ እንዲህ እንደተባለ፡ “የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክን ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን?” ሃዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም “ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም።”(1ቆሮ 2:11) በማለት እንደተናገረ ማለት ነው። ሊታወቅ የሚችለው እርሱ ራሱን በገለጠበት ልክ ነው። ይህ የእግዚአብሔር መገለጥ ይባላል። የእግዚአብሔር መገለጥ ስንል ፈጣሪ ራሱን ለፍጥረቱ በተለይም ለሰዎች የገለጠበት መንገድ እያልን ነው። የአንድ ሃይማኖት መሰረቱም የእግዚአብሔር መገለጥ ነው። እግዚአብሔር ራሱን ባልገለጠበት መልኩ እኛ ልናውቀው አንችልምና። ስለዚህ “መገለጥ ማለት በማይወሰነው ኃያል አምላክ እና ውስን በሆነው ሰው መካከል ያለ ግንኙነት ማለት ነው።” መገለጡ ፍሬያማ የሚሆነው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል መግባባት ሲኖር ነውና የሰው አቅም በሚችለው መልኩ በሰው መግባቢያ ቋንቋዎችና በሌሎች መንገዶችም እግዚአብሔር ወርዶ ራሱን ይገልጣል ማለት ነው ይሉናል ዶክተር ጆሲ ጃኮብ የተባሉ አንድ የሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባት። ስለዚህም እግዚአብሔርን የምናውቀው በመገለጡ(ἐνέργεια - energies) ብቻ ነው። ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ብቻ ሳይሆን ደግሞ በሕይወታችንም ውስጥ እግዚአብሔርን ልናየው ልናውቀው አብረነው ልንኖር ይገባልና እንዲህ ያለውን ከፍ ያለውን ነገር ለማየት ደግሞ ከቅዱስ ምስጢር(ቁርባን) በየጊዜው ልንሳተፍ ይገባል።

ለምሳሌ ጸሐይ ምን ያህል ትሞቃለች ብንል ምናልባት እያንዳንዳችን እንዳለንበት አካባቢ 24°C ፣ 35 °C እያልን እንመልስ ይሆናል። ውኃን በእሳት ስናፈላ መፍላት የሚጀምረው በ100 °C ነው። 100 °C ውኃ የማፍላት ያህል ሙቀት ካለው 1000 °C ወይም ደግሞ በጣም ከፍ አድርገን 100,000 °C ምን ዓይነት ሙቀት ይኖረው ይሆን..?? እዚህ ላይ አንድ ነገር እናስተውል.. ቀደም ብለን የጸሐይ ሙቀት ብለን ያነሳነው ላይ 24 እና 35°C ብለን ስንናገር ጸሐይ እኛ ጋር የደረሰችበት ወይም ደግሞ እንበለውና ራሷን ለእኛ የገለጠችበት የሙቀት መጠንን ይዘን እንጂ ምናልባት ጠጋ ብንላት በሚያስገርም ሁኔታ ሙቀቷ ከ15,000,000(15 ሚሊዮን) °C በላይ እደሆነ ይነገራል። ያው እኛ ግን የምናውቃት ለእኛ በምንችለው መጠን በወረደችበት ወይም በደረሰችበት ሙቀት ያህል ነው። እንደዚሁ አምላክ እግዚአብሔርም የሚታወቀው እኛ በምንችለው ልክ እራሱን በገለጠው ልክ ነው። ጸሐይ ለእኛ የተገለጠችበትን የሙቀት መጠን ይዘን የጸሐይ ትክክለኛው ሙቀትም ይኼው ነው ብለን እንደማንወስን እንዲሁ ደግሞ እግዚአብሔር እኛ በምንረዳው ልክ ዝቅ ብሎ ሲገለጥልን በዚህ መገለጥ ልንወስነው አንችልም። ይህም ማለት ለእግዚአብሔር የተነገሩ ቃላትን ሁሉ ለባህሪው ሰጥተን ልንናገር አይገባም። ለዛም ነው ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ እንዲህ ያለው፡ “ምናልባት አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር የተነገረበት ሰዋዊ አነጋገር(Metaphor) ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርግ ከሆነ ይህንን ጌታ በተሳሳተ መልኩ በመግለጽ ይስታል።”[1]

## የእግዚአብሔርን መገለጥ ከየት ልናገኝ እንችላለን..??

እግዚአብሔር ራሱን በሁለት መንገድ ይገልጣል እነርዚህም አጠቃላይ መገለጥ እና ልዩ መገለጥ ናቸው። በአጠቃላይ መገለጥ ውስጥ በዋናነት እግዚአብሔር ራሱን በፍጥረቱ በኩል የገለጠበት መንገድ ነው.. ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል ፡ “እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና” [ሮሜ 1 ፡ 19-20] መዝሙረኛውም እንዲህ ይላሉ ፡ “ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።”[መዝ 19፡ 1] ስለዚህም አምላክ ከፍጥረቱ በማንኛውም ሰው ክርስቲያን ባልሆነም ጭምር ሊታወቅ ይችላል። ምክንያቱም እንዲህ ያለው መገለጥ አጠቃላይ መገለጥ ነውና.. ሁለተኛው የመገለጥ መንገድ ግን ልዩ መገለጥ ነው ይህም በአጭሩ ዕብራውያን 1 ፡ 1 ላይ እንዳለው ነው ፡ “ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፤ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን” ይህ መገለጥ ልዩ መገለጥ ይባላል የመገለጥም ደግሞ ፍጻሜው በልጁ በኢየሱስ በኩል ያደረገው መገለጥ ነው። “መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድስ እንኳን የለም በእቅፉ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው”[ዮሐ 1:18] እንዲል።

---

[1] St. Ephrem the Syrian: Hymns on Paradise, 11:6 [Dr. sebastean brock]

ይህ እንዳለ ሆኖ በአጠቃላይ መገለጥ(general revelation) ውስጥ የሚታየውን የፈጣሪን መኖር አንስተን የተወሰነ ወደ መመልከቱ እናልፍና ወደ ኋላ ደግሞ ከዚሁ አምላክ በልዩ መገለጥ ውስጥ የተላለፈውን ሃይማኖት ወይም መገለጥ የምንመለከት ይሆናል።

## 1. kalam cosmological argument - KCA(ካላም)

- ህልውናው የጀመረ ነገር ሁሉ አስጀማሪ(cause) አለው
- የዓለማት(universe) ህልውና የጀመረ ነው
- ስለዚህ የዓለማትን ህልውና ያስጀመረ አለ

የመጀመሪያው ቅድመ አሳብ ላይ “መኖር የጀመረ ነገረ ሁሉ አስጀማሪ አለው” የሚለው መቼስ ግልጽ እንደሆነ አስባለሁ.. ምንም ዓይነት ነገር ካለመኖር ወደ መኖር ከመጣ የሆነ ያመጣው አንዳች ነገር ይኖራል እንጂ በራሱ እንዲሁ ከምንም ብቅ የሚል የለም። ለምሳሌ ይህንን የምታነበው አንተ ወዳጄ መኖር ለመጀመርህ ምክንያቶች አሉህ.. ለምሳሌ ወላጆችህ.. እጄ ላይ ያለው ኮምፒዩተርም እንዲሁ በራሱ አልመጣም.. የሚታየውም የማይታየውም ግን ደግሞ ሕልውናው የጀመረ ነገር ሁሉ አስጀማሪ አለው። ለምሳሌ የሆነ ነገር ወደ ሕልውና ቢመጣና ያ ነገር ማንኪያ ቢሆን አንድ ጥያቄ እንጠይቃለን.. ይህ ነገር ለምን ድመት አልሆነም..?? ወይም ለምን ፓስታ አልሆነም..?? ይሄ ደግሞ ወዴት ያመራናል ካልን ድመት ወይም ፓስታ ሳይሆን ማንኪያ የሆነበት ምክንያት ይህ ይህ ነው ወደሚል ትንታኔ እንድናልፍ ያደርገናል.. በዚህ ውስጥ ማንኪያ እንዲሆን ያደረገውን ምክንያት እናውቃለን.. ያ ምክንያት ለማንኪያው መፈጠር ምክንያት ወይም አስጀማሪው ነው።

ሌላው እዛው የመጀመሪያው ቅድመ አሳብ ላይ ልናስተውል የሚገባው ነገር “ሕልውና ያለው ነገር ሁሉ አስጀማሪ(cause) አለው” አይደለም የሚለው.. “ሕልውና ያለው” ሳይሆን “ሕልውናው የጀመረ” ነው የሚለው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ሕልውና አለው ግን ደግሞ ሕልውናው የጀመረ ሳይሆን ከጊዜ ውጪ ስለሆነ ይህ ነገር እርሱን እንደማይመለከት ልብ ይሏል። እንዴት ከጊዜ ውጪ ይሆናል የሚለውን ከታች እንመለከታለን።

ሁለተኛው ቅድመ አሳብ ደግሞ “ዓለም መኖር የጀመረ ነው” የሚል ነው.. ዓለም(universe) ስንል ደግሞ ጊዜን እና ቦታን ጨምሮ በዓይናችን የምናያቸውንና የማናያቸውን ነገሮች ሁሉ ያጠቃልላል (time, space, matter and energy)። ግን ደግሞ ይህ ዓለም መኖር **የጀመረ ሳይሆን** ከዘላለምም(infinitely ወይም ያለ ገደብ ማለቂያ በሌለው ጊዜ ውስጥ) የነበረ ቢሆንስ..?? ይህ ፍጹም ሊሆን የማችልበትን ምክንያት ላሳያችሁ.. እዚህ ላይ የዓለምን ሕልውና ወደ ኋላ ስናስበው ጊዜው infinite(ምንም ማለቂያ የሌለው ዘላለም) ነው የሚለውን አሳብ ለማፍረስ የ big bang(ቢግ ባንግ) cosmological theoryን ለመጠቀም የሚሞክሩ ሰዎች አሉ.. ቢግ ባንግ ሳይንሳዊ አሳብ ሲሆን በአጭሩ እንዲህ ይላል፡ ዓለም የተፈጠረው ከ10 እስከ 20 ቢሊየን ዓመት በፊት ከጥቂት መጠነ ቁስ ፍንዳታ ነው የሚል ነው። ስለዚህም በዚህ ሳይንስ አሳብ ዓለም መኖር የጀመረ እንጂ ከዘላለምም ያለ አልነበረም ማለት ነው። እኛ ግን የምንጠቀመው ለጊዜው እንዲህ ያለውን ግምታዊ አሳብ ሳይሆን አንድ ፍልስፍናዊ የሙግት መንገድ በመጠቀም ይሆናል.. እንዴት..?? ለምሳሌ ይህንን ጽሑፍ አንብባችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ አንድ መጽሐፍ ማንበብ እንደምትጀምሩ ብትወስኑና ማንበብ ብትጀምሩ ያው ጽሑፏ አነስ ያለች ከመሆኗ አንጻር ቶሎ ትጨርሷታቻችሁ.. ግን ደግሞ ጽሑፉ ተለቅ ያለ መጽሐፍ ሆኖ 1400 ገጽ ቢሆንስ..?? ምናልባት ዓመትም ይፍጅብህ ወይም ደግሞ ስልቹ ሆነህ 10 ዓመትም ይፍጅብህ ጨርሰህ ወዳቀድከው ቀጣዩ መጽሐፍ ትሻገራለህ.. መልካም.. እንበለውና መጽሐፉ ግን infinitely ብዙ ገጽ ሆኖ በገለጥከው ቁጥር ጭራሽ የማያልቅ ቢሆን ይህንን መጽሐፍ ጨርሰህ ልታነበው አትችልም.. ይህንን አንብበህ ካልጨረስክ ደግሞ ይህንን ስትጨርስ ልታነበው ያቀድከውን ሌላኛውን መጽሐፍ ልታነብ አትችልም ማለት ነው። ይህንን ያነሳሁት ለምንድን ነው.. ለምሳሌ የዛሬዋ ቀን ትደርስ ዘንድ ቀድመው ያለፉ በርካታ ቀናት አሉ.. ያለፉት ቀናት ሚሊዮን ወይም ቢሊዮን ያህል ቀናት ቢሆኑ ያው እኚህ ሁሉ ቀናት አልፈው የዛሬዋ ቀን ደረሰች እንል ይሆናል.. ግን ደግሞ ያለፉት ቀናት ቀናት ቢሊዮን ብቻ ሳይሆን infinite ከሆነ ከላይ እንዳልኳችሁ infinite ደግሞ የማያልቅ ስለሆነ ዛሬ ራሱ ልትደርስ ባልቻለች ነበር.. ግን ደግሞ ዛሬ ቀን ይኸው ደርሶ አይተናል ስለዚህም ዛሬን የሚቀድመው ጊዜ infinite ሊሆን አይችልም.. ስለዚህም ዓለም የሆነ የጀመረበት ጊዜ አለ።

ሦስተኛው ወይም መደምደሚያው አሳብ የዓለማት ሕለውና የጀመረ ከሆነ እንግዲያውስ አስጀማሪ አለው የሚል ስለሆነ ይህ አስጀማሪ እርሱ ነው ፈጣሪ ብለን መያዝ እንችላለን። ይህ አስጀማሪ(ፈጣሪ) ግን ዓለማትን አስጀምሮ ከዚያም የጠፋ ቢሆንስ..?? ይህ ሊሆን አይችልም ምክኒያቱም አስጀማሪውን ጊዜ ውስጥ መክተት ስለሆነ የሚሆንብን.. ጊዜና ቦታን ያስጀመረ እርሱ ከጊዜም ከቦታም ውጪ ስለሆነ በዚህ ጊዜ ጠፋ ማለት አንችልም። ሌላ ጥያቄ እዚሁ ላይ.. ይህ አስጀማሪ የሆነ ኃይል ነገር ብቻ እንጂ አካል ወይም ማንነት የሌለው ነገር ቢሆንስ..?? ይህም ሊሆን አይችልም ምክንያቱም አስጀማሪው ዓለማትን አሁን ባለው መልኩ እንዲሆን አድርጎ መርጦ አስጀምሯልና አካላዊ ወይም ማንነት ያለው እንደሆነ ያሳያል.. ምክንያቱም እንዲሁ ማንነት የሌለው ኃይል የሆነ ነገር ምርጦ አቅዶ የሚያደርገው ነገር ስለማይኖር። ሌላ ጥያቄ እዚሁ ጋር.. ይህ አስጀማሪ(ፈጣሪ) ምን ያህል ኃያል እንደሆነስ ያሳያል..?? ምን ያህል ኃያል እንደ ሆነ ወይም የኃይሉን ጥግ አያሳይም.. ቢያንስ ግን ዓለማትን ካለመኖር ወደ መኖር እስኪያመጣ ድረስ ኃያል እንደ ሆነ ያሳያል.. እንደ ክርስቲያን የኃያልነቱን መጨረሻ ማወቁንም አንፈልገውም ምክኒያቱም ፈጣሪን እንደው በገለጠልን ልክ እናውቀው ይሆናል እንጂ በባህሪው

ልናውቀውም ስለማንችል.. ስለዚህ ጉዳይ ወደ ኋላ ጥቂት ነገሮችን እናያለን። የመጨረሻ ጥያቄ.. ይህ አስጀማሪ ሥላሴ መሆኑንስ ከዚህ አመክንዮ(KCA) መረዳት እንችላለን..?? አንችልም ይህ አመክንዮ ዋናው አሳቡ መኖር የጀመሩ ነገሮችን ሁሉ ያስጀመረ ፈጠሪ መኖሩን ማሳየት እንጂ ያ ፈጣሪ ሥላሴ ይሁን ወይም በእስልምና ውስጥ አምላክ ተብሎ የሚታወቀው ይሁን ወይም 18 አማልክት ይሁኑ አያብራራም። እውነተኛው አምላክ የክርስቲያኖች አምላክ እንደሆነም ወደ ኋላ ጥቂት ነገርን አስቀምጥላችኋላው.. ለጊዜው ግን ፈጣሪ መኖሩን እንደሚያስረዳ ብቻ እንወቅ።

## 2. The design Argument:

አንድ ትልቅ የሚያምር ሕንጻ ስታዩ ያ ሕንጻ እንዲሁ በድንገት እንደ እድል ሆኖ በዚህ መልኩ እንደ በቀለ ታስባላችሁ ወይስ ሕንጻው እንዲህ እንዲሆን ያደረገው የሆነ ዲዛይነር እንዳለ ታስባላችሁ..?? የጌታችን ኢየሱስን የስቅለት ስእል ስታዩ ስእሉ እንዲሁ ቀለም ሲደፋ እንደው አጋጣሚ እንዲህ ሆነ ትላላችሁ ወይስ ከወንጌል ጋር እንዲስማማ አድርጎ የሳለው ሰአሊ እንዳለ ታስባላችሁ..??

ይህንን ያነሳሁት ተፈጥሮን ስናይ የምናያቸውና የምናስተውላቸው ነገሮች እንዲሁ እንደ እድል የተገኙ ሳይሆን ይልቁንም በሆነ ዲዛይነር የተበጀጀ እንደሆነ አመላካች ነው። ለምሳሌ እስቲ ዓይናችን እንዴት እንደሚሰራ አጠር አድርጌ ላሳያችሁ




አሁን ይህንን ጽሑፍ ስታዩ አይናችሁ እና አእምሮዋችሁ ላይ ብዙ ሥራ እየተሰራ ነው። ይህንን ጽሑፍ ስታዩ መጀመሪያ ብርሃን ቀጥታ በውጨኛው የዓይናችን ክፍል ኮርኒያ(cornea) በኩል ይገባና ያ ብርሃን ፐዩፒል(pupil) በተባለ ክፍተት ወስጥ ይገባል.. በፐዩፒል በኩል የገባውን ብርሃን ደግሞ አይሪስ(iris) የተባለው ክፍል ምን ያህል መግባት እንዳለበት ይመጥናል። ከዚያም ያ ተመጥኖ ያለፈው ብርሃን ሬቲና(retina) ላይ ሲያርፍ ፎቶሪሴፐተርስ በተባለ ሴል ከብርሃንነት ወደ ኤሌክትሪካል ሲግናልነት ይለወጣል። ከዚያም ያ የተለወጠው ኤሌክትሪካል ሲግናል በኦፕቲክ ነርቭ(Optic nerve) በኩል ወደ አእምሮ ይሄድና አእምሮ ፊትለፊት ላይ ወደምታዩት ወደዚህ ወደምታዩት ጽሑፍ ይቀይረዋል።

መልካም እዚህ ላይ ጥያቄው.. እንዲህ ያለ ውስብስብ ነገር ተከናውኖ እናያለን.. ታድያ ይህ ሁሉ ነገር እንደው እንደ እድል ነው የሆነው ወይስ ሰሪ አለው..?? መቼስ አጋጣሚ ብርሃን መጥቶ በኮርኒያ አልፎ በኋላ ሬቲና ላይ ተቀይሮ ከዚያም ወደ አእምሮ ሄዶ ተረዳነው ማለት ጭራሽ አይታሰብም። ይህ ነገር በእርግጥም ሠሪን ያመለክታል በግልጽ። የሆነ ሠሪ በዚህ መልኩ እንዲሆን አበጃጅቶታል።

ሌላ ተጨማሪ ነገር ልንገራችሁ.. ለምሳሌ እኛ ለመኖር ኦክሲጅን የተባለ አየርን ወደ ውስጥ እናስገባለን.. ይህንን ኦክሲጅን ከእጸዋት እናገኛለን.. እነርሱም ደግሞ ካርቦን ዳይኦክሳይድን ወደ ውስጥ ያስገባሉ.. እህንን ደግሞ ከእኛ ያገኛሉ ምክንያቱም ከእኛ የሚወጣው ካርቦን ዳይኦክሳይድ ነው። እውን ይህ በእድል የተፈጠረ ወይስ እንዲህ እንዲሆን ተደርጎ በሆነ ግሩም ሠሪ የተበጃጀ..??

አጠቃላይ ምድር እኛ እንድንኖርባት ምቹ መሆኗ በእድል..?? ብዙ ነገሮችን እንዲሁ እንደ እድል ተከሰተ ካልን ከእኛ የሚበልጥ ምስኪንም ፈጣሪን ላለማወቅ የወሰነም አይኖርም በእውነት።

ስለዚህም ዓለም ዲዛይነር አላት እኛም አምላክ የምንለው ያንን ዲዛይን የተደረጉትን ሁሉ ዲዛይን ያደረገውን ነው።

## 3. ትራንሰንደንታል አርግዩመንት(transcendental argument)

ይህ ደግሞ በአጭሩ በእኛ ዘንድ ሕሊና ወይም morality(ሞራሊቲ) የሚባል ነገር አለ። ለምሳሌ መስረቅ መግደል መድፈር እና የመሳሰሉት ነገሮች ትክክል እንዳልሆኑ እናውቃለን.. ምክንያቱም ሕሊና አለን። የምርም ሕሊና ካለ ደግሞ የዛ ሕሊና ምንጩ ማን ነው..?? ራሱ እግዚአብሔር ነው የሚል ነው ይህ የሙግት አሳብ። በአጭሩ እዚህ ላይ ላቋርጠው ይህንን።